እንኳን ደህና መጣችሁ

ሚያዚያ/2013

ከንግድ ስራ እና ከኪራይ
ገቢ የሚገኝ ግብር

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ሞጁል ሁለት
ከቤት ኪራይ እና ከንግድ ስራ የሚገኝ ገቢ ግብር ማሠልጠኛ ሰነድ

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

የሰነዱ ይዘት

• ክፍል አንድ ፡ - አጠቃላይ ሁኔታ
• ክፍል ሁለት ፡ - የቤት ኪራይ ገቢ ግብር(ሰንጠ፣ለ)
• ክፍል ሦስት፡- የንግድ ስራ ገቢ ግብር (ሐ)
• ክፍል አራት፡- የሂሳብ መዝገብ አያያዝ
• ክፍል አምስት፡- ድርጅትን በመቆጣጠር ረገድ የሚደረግ

ለውጥ

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ክፍል አንድ

1. አጠቃላይ ሁኔታ
1.1. ዓላማ
1.1.1. ዋና ዓላማ፤
 ከሥልጠናው በኋላ ሠልጣኞች፤
• የገቢ ግብር የሚከፈልባቸውን የሰንጠረዥ ለ የኪራይ ገቢ ግብር እና “ “ የሰንጠረዥ ሐ የንግድ ሥራ ገቢ ግብሮች “ “ በታክስ ሕግ በተቀመጠው አሠራር መሠረት ግብራቸውን አሳውቀው መክፈል እንዳለባቸው በሥልጠና ላይ በሚደረግ ውይይት ይረዳሉ፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

1.1.2. ዝርዝር ዓላማ፤
• የኪራይ ገቢ ግብር መጣኔዎችን በማስላት ያሳያሉ፤
• በገቢ ግብር አዋጅ የተካተቱትን የሰንጠረዥ ለ ገቢዎችን “ “

ምንነት ይገልጻሉ

• የማይሰበሰብ እዳ በተቀናሽነት ሊያዝ የሚችለው ምን፤ምን መስፈርቶች ሲሟሉ እንደሆነ ያብራራሉ
• በአንድ የግር ዘመን ኪሳራ የገጠመው ሰው ኪሳራውን የሚያሸጋግረው ለስንት አመታት እንደሆነ ይገልጻሉ

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ዝርዝር አላማ

• ለረጅም ጊዜ ከተደረገ ውል ጋር ተያይዞ ግብር ከፋዩ
ኪሳራ ቢያጋጥመው ኪሳራውን እንዴት እንደሚያሸጋግር ያብራራሉ

• የንግድ ስራ ከተቋረጠ በኋላ በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር

እንዴት እንደሚወሰን ያስረዳሉ

• ከግብር መሸሽ (tax avoidance) እና ግብር
መሰወር (tax evasion) መካከል ያለውን ልዩነት
ያብራራሉ

• የዕርጅና ቅናሽ ዘዴዎችን እና ስሌቶችን በምሳሌ
ያስረዳሉ

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

1.2. ሥልጠናው የሚወስደው ጊዜ

•ይህን ሥልጠና ለማሠልጠን 18 ሰዓት ይጠይቃል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

1.3. ትርጓሜ…

የንግድ ስራ ማለት፡ -
•በተከታታይ ወይም ለአጭር ጊዜ ለትርፍ የሚከናወን ማኛውም የኢንዱስትሪ፣የንግድ፣የሙያ፣ወይም ቮኬሽናል ስራ ሲሆን ተቀጣሪ ለቀጣሪው የሚሰጠው አገልግሎት ወይም ቤት ማከራየትን አይጨምርም፣በንግድ ህግ መሰረት የንግድ ስራ ነው ተብሎ እውቅና የተሰጠው ሌላ ማኛውም ስራ፣ ህንጻ ማከራየትን ሳይጨምር የኩባንያው አላማ ምንም ቢሆን ማንኛውንም የአክሲዮን ማህበር ወይም ኃ.የተ.የግ.ማህበር የሚሰራው ማንኛውም ስራ፤

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ትርጓሜ…

ግብር የሚከፈልበት የኪራይ ገቢ ማለት፡ -
• በግብር ዓመቱ ግብር ከፋዩ ቤት በማከራየት ካገኘው ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ ላይ ለግብር ከፋዩ የተፈቀደው ጠቅላላ ወጪ ተቀናሽ ተደርጎ የሚቀረው ገቢ ነው፡፡

የንግድ ስራ ሃብት ማለት፡ -
• የንግድ ስራ በማከናወን ሂደት በሙሉ ወይም በከፊል የንግድ ስራ ገቢ ለማግኘት የተያዘ ወይም ጥቅም ላይ የዋለ ሀብት ነው፤

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ትርጓሜ…

ራሱን የቻለ ስራ ተቋራጭ ማለት፡ -
• ስራውን በአመዛኙ በራሱ የመምራት እና የመቆጣጠር በቂ ስልጣን በሚሰጠው ውል መሰረት አገልግሎት የሚሰጥ ግለሰብ ነው፤

የቴክኒክ ክፍያ ማለት፡ -
• ለቴክኒካዊ፣ሙያዊ፣ወይም ለማማከር አገልግሎት የሚከፈል ክፍያ ነው፤

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ትርጓሜ…

የንግድ እቃ ማለት፡ -
• ማንኛውም የተመረተ፣ የተፈበረከ፣ የተገዛ፣ ወይም ለማምረት፣ ለመሸጥ ወይም ለመለወጥ በማናቸውም ሁኔታ የተገኘ ዕቃ፤ በማምረት ወይም በመፈብረክ ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም ጥሬ ዕቃ ወይም አላቂ ዕቃ ወይም ለጭነት ወይም ለስራ የሚያገለግሉ እንስሳትን ሳይጨምር ማንኛውም እንስሳ፤

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

1.4 ታክስ የመጣልና የማስከፈል ሥልጣን

 ከታክስ የሚሰበሰብ ገቢ ለአንድ መንግስት ህልውና እጅግ አስፈላጊ

ስለሆነ ታክስ የመጣልና የማስከፈል ሥልጣን ለመንግስት ብቻ የተሰጠ ሥልጣን ነው፡፡

 ለግለሰብ ወይም ለሌላ አካል የዚህ ዓይነት ሥልጣን በየትኛውም ዓለም

አይሰጥም፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ታክስ የመጣልና …

 የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ለፌደራል መንግስት በህገ መንግስቱ

በተሰጠው ታክስና ግብር የመጣልና የማስከፈል ሥልጣን መሠረት

በሁለት መሠረታዊ የታክስ አጣጣል መሠረቶች (ወሰኖች) የታክስ ህግ ድንጋጌዎችን የሚያስቀምጥ ሲሆን እነዚህም፤
ሀ. ነዋሪነትን መሠረት ማድረግ፣
ለ. የገቢ ምንጭን መሠረት ማድረግ ናቸው፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

1.5.ታክስ ለማስከፈል የህጉ ተፈጻሚነት ወሰን

 የኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች በዓለም ዙሪያ በሚያገኙት ገቢ

እንዲሁም

 ኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎች የኢትዮጵያ ምንጭ በሆነ ገቢ ላይ ግብር የሚጣልባቸው ሲሆን ፣አከፋፈሉን፣አወሳሰኑንና አሰባሰቡም ተፈጻሚ ይደረጋል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ሀ. ነዋሪነት
ነዋሪ የሆነ ግለሰብ
•ኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ የመኖሪያ አድራሻ (domicile)

ያለው፣

•በመንግስት ተመድቦ በውጭ አገር የሚሠራ ኢትዮጵያዊ ዜጋ፣ •በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በተከታታይ ሳያቋርጥ ወይም በመመላለስ ከ 183 ቀናት በላይ የኖረ ግለሰብ፣

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ሀ. ነዋሪነት

ነዋሪ የሆነ ድርጅት
• ኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመ /የተመሠረተ/፣
• ወሳኝ የሆነ የሥራ አመራር የሚሰጥበት ሥፍራ ኢትዮጵያ ውስጥ

ያለው፣

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ለ. የገቢ ምንጭ

 በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያፈራው የንግድ

ሥራ ገቢ

 (ነዋሪ የሆነ ሰው በውጭ አገር ባለው በቋሚነት በሚሠራ ድርጅቱ
አማካኝነት ከውጭ አገር የሚያገኘው ገቢ ከውጭ ምንጭ የተገኘ ገቢ ነው

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

1.5.1. ኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ ሰው፣

 በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚያካሂደው

የንግድ ሥራ የሚያገኘው ገቢ፣

 በቋሚነት የሚሠራው ድርጅቱ ከሚያስተላልፋቸው ዕቃዎች ወይም ሸቀጦች ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሣሣይ የሆኑ ዕቃዎችን ወይም ሸቀጦችን ኢትዮጵያ ውስጥ በቀጥታ በማስተላለፍ የሚያገኘው ገቢ፣

 በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ከሚያከናውናቸው ማናቸውም የንግድ ሥራዎች ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሣሣይ የሆኑ ሌሎች የንግድ ሥራ

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ክፍል ሁለት

2. የቤት ኪራይ ገቢ ግብር (ሠንጠረዥ “ለ“)

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

2.1 የቤት ኪራይ ገቢ ግብር ስለመጣል 13-14

ግብሩ በየዓመቱ በሚገኝ ገቢ ላይ ይጥላል፣
ግብሩ የሚጣለው ለግለሰብ እና ለድርጅት በተለያዩ መጣኔዎች ግብሩ ቤት ወይም ህንፃ በማከራየት ገቢ በሚያገኝ ሰው ላይ

ይጥላል፣

ታክሱ ሊጣል የሚችለው በግብር ዘመኑ ታክስ የሚከፈልበት ገቢ ከተገኘ ነው፤

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

2.2. የቤትኪራይ ገቢ

ግብር የሚከፈልበት የኪራይ ገቢ የሚባለው
•በግብር ዓመቱ ግብር ከፋዩ ቤት በማከራየት ካገኘው ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ ላይ

•ለግብር ከፋዩ የተፈቀደው ጠቅላላ ወጪ ተቀናሽ

ተደርጎ የሚቀረው ገቢ ነው፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

የቤትኪራይ ገቢ …

ቤት በማከራየት የሚገኝ ጠቅላላ ገቢ የሚከተሉትን

ይጨምራል፡፡

•የኪራይ ዋጋ ጭማሪን (premium)፣
•ተመሳሳይ ክፍያዎችን ጨምሮ በኪራይ ውሉ መሠረት
ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ የሚያገኘው ማናቸውም የገንዘብ መጠን፣

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

የቤት ኪራይ ገቢ …

 ተከራይ አከራዩን በመወከል በግብር ዓመቱ ለሌሎች የሚከፍላቸው ክፍያዎች፣
 ለጉዳት ማስተካከያ ይሆን ዘንድ ግብር ከፋዩ የያዘውና ያልተጠቀመበት ለግብር ከፋዩ ገቢ የተደረገው ማናቸውም ገቢ

 ግብር ከፋዩ ቤቱን ያከራየው ከዕቃዎች ጋር በሚሆንበት ጊዜ ያገኘው ጠቅላላ ገቢ ከዕቃዎቹ የተገኘውን የኪራይ ገቢም ያጠቃልላል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

2.3. ተቀናሽ የሚደረጉ ወጪዎች የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ለሌለበት ግብር

ከፋይ
•ታክስን ሳይጨምር ለመሬቱ ወይም ከተከራየው ቤት ጋር በተገናኘ ግብር ከፋዩ ለከተማ አስተዳደር የከፈላቸው ክፍያዎች፣
•ከቤት ዕቃና ከመሣሪያ ኪራይ ከሚገኘው ጠቅላላ ገንዘብ ላይ 50% በመቶ፣(ለቤቶች፣ለቤት ዕቃና መሳሪያ ማደሻ፣መጠገኛና ለእርጅና መተኪያ የሚሆን)
ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ተቀናሽ የሚደረጉ …

የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት ግብር

ከፋይ
• ገቢውን ለማግኘት የወጣና በግብር ከፋዩ የተከፈለ አስፈላጊ የሆኑ (ገቢውን ለማግኘት፣ ዋስትና ለመስጠት እና ሥራውን ለማሰቀጠል ወጪዎች ተቀናሽ ይደረጋሉ፤

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ተቀናሽ የሚደረጉ …

• ቤቱ ያረፈበት የመሬት ኪራይ ፣የጥገና ወጪ፣ የእርጅና ቅናሽ፣

ወለድና የመድን አርቦን፣ ታክስን ሳይጨምር ለመሬቱ ወይም ከተከራየው ቤት ጋር በተገናኘ ግብር ከፋዩ ለከተማ አስተዳደር የከፈላቸው ክፍያዎች
• በነፃ ወይም በኪራይ የያዘው ቤት ስም የሚከፈል የውሃ፣ የስልክ፣የመብራት ወጪዎች በውሉ ተከራይ እንዲከፍሉ ከተገለፁ ወጪው ስለማውጣቱ ደረሰኝ ካቀረበ ይያዝለታል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ተቀናሽ የሚደረጉ …

• የኪራይ ቤቱ እና የመኖሪያው ቤት በአንድ የመብራት፣ የስልክ፣ የውሃ ቆጣሪ የሚጠቀሙ ከሆነ ለነዚህ የወጣው ወጪ 75 በመቶ በወጪነት ተቀናሽ ሊያዝ ይችላል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ተቀናሽ የሚደረጉ …

• በብድር ለተገኘ ወለድ ክፍያ በወጪነት የሚያዘው ለኪራይ አገልግሎት

ብቻ መጠን ልክ ነው፤

• ለኪራይ የሚያስገነባው ህንጻ ብድር የተወሰደ ከሆነ እና የብድር ወለድ ወጪ የሚያዘው፡-
• ህንፃው እሰስኪገነባ ድረስ ያለው የህንፃው ዋጋ ሆኖ በእርጅና ቅናሽ የሚታሰብ ሲሆን፤
• ህንፃው ተገንብቶ ከተጠናቀቀ በኃላ በወጪነት የሚፈቀድ ይሆናል፤

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ተቀናሽ የሚደረጉ …

 ኪራይ አገልግሎቱን ለማስተዋወቅ የሚወጣ ወጪ

የሚያዘው፡-

•በተለያየ ዝግጅት ላይ ለሚደረግ የማስታወቅ ሲሆን ከጠቅልላላው ኪራይ ገቢ 3 በመቶ ባልበለጠ፣
•ለመገናኛ ብዙሃን ወይም ለማስታወቂያ ድረጅት ከሆነ

በሙሉ ተቀናሽ ይሆናል፤

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን



ተቀናሽ የሚደረጉ …

 ለኪራይ የተገነባው ህንፃ ለሌላ ዓላማ ዕስካልዋለ ድረስ ግብር ከፋዩ ህንፃውን ለኪራይ አገልግሎት ዝግጁ ያደረገ ከሆነ ህንፃው ባይከራይም ለኪራይ እንደዋለ ተቆጥሮ እርጅና ቅናሹ እንደ ወጪ ይያዛል፤

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ተቀናሽ የሚደረጉ …

አንድ ህንፃ
• ለኪራይ አገልግሎት እና ለሌላ ገቢ ለማስገኘት የዋለ እንደሆነ የወጪው ክፍፍል ጥቅም ላይ በዋለበትና በገቢው ድርሻ ልክ ነው፤

• ለሌላ አገልግሎት ከዋለ የእርጅና ቅናሹ ወጪው ተለይቶ መቅረብ አለበት፤ ተለይቶ ካልቀረበ ከጠቅላላው የህንፃ ዋጋ ለኪ ራይ አገልግሎት የዋለውን ስፋት መጠን በማስላት ተቀናሽ ይደረጋል፤

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ተቀናሽ የሚደረጉ …

 ለእርጅና ቅናሽ ለማስላት መሠረት ሚሆነው ዋጋ፡ - •ለኪራይ የዋለው ህንፃ የተሰራበት ወይም የተገዛበት ዋጋ

ነው ወይም

•ይህ ካልቀረበ ህንፃው የተሰራበት /የተገዛበት የገበያ ዋጋ 70 በመቶ በመያዝ የዕርጅና ቅናሽ ይሰላል፤

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ተቀናሽ የሚደረጉ …

 ለእርጅና ቅናሽ ለማስላት መሠረት ሚሆነው የተገዛበት /የተሰራበት ዋጋ የተጨማሪ እሴት ታክስ በግብዓትነት የተካካሰለት ከሆነ በተካካሰው መጠን ልክ ከእርጅና ቅናሽ መሰረት ከሆነው ዋጋ ውስጥ መቀነስ አለበት፤

 በታክስ ከፋዩ ስም ላልተመዘገቡ ሀብቶች የእርጅና ተቀናሽ ወጪ አይፈቀድም፤የሚፈቀደው ስልጣን በተሰጠው አካል ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ነው ፤

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ተቀናሽ የሚደረጉ …

 በባል ወይም በሚስት ለተመዘገበ ህንፃ ህንፃው ለኪራይ አገልግሎት እንዲውል፣ተቀናሽ እንዲጠየቀበትና ህንፃው ሲሸጥ ተገቢው ግብርና ታክስ እንዲከፈልበት የባልና ሚስት ስምምነት ሰነድ ሲቀርብ ነው፡፤

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

2.4. የኪራይ ገቢ ግብር ማስከፈያ መጣኔ

ለድርጅቶች የኪራይ ገቢ ግብር መጣኔ 30% (ሰላሳ በመቶ) ነው፡፡
ለግለሰቦች በሠንተረዥ 1 መሰረት ከ10 እስከ 35 በመቶ በሚደርስ መጣኔ ግብር ይከፍላሉ፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

2.4.1.ለግለሰብ የኪራይ ገቢ ግብር መጣኔ

ግብር የሚከፈልበት የኪራይ ገቢ
በዓመት

የኪራይ ገቢ ግብር
መጣኔ

ተቀናሽ

0 7,200 0% 0
7,201 19,800 10% 720
19,801 38,400 15% 1,710
38,401 63,000 20% 3,630
63,001 93,600 25% 6,780
93,601 130,800 30% 11,460
ከ130,801 በላይ 35% 18,000

ሠንጠረዥ 1 የግለሰብ የኪራይ ገቢ ግብር መጣኔ

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

2.5. የተከራይ አከራዮች

 የተከራይ አከራይ በግብር ዓመቱ ያገኘው ግብር

የሚከፈልበት ገቢ ነው የሚባለው፡ -
•በግብር ዓመቱ ከተቀበለው ጠቅላላ የኪራይ ገቢ ላይ
•ለዋናው አከራይ የሚከፍለው ኪራይ
•እንዲሁም ገቢውን ለማግኘት ያወጣቸው ሌሎች ወጪዎች

ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው ገንዘብ ነው፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

የተከራይ አከራዮች …

 ተከራይ የተከራየውን ቤት መልሶ እንዲያከራይ የሚፈቅድ የቤት ባለቤት ተከራዩ ግብሩን ሳይከፍል ቢቀር ስለእርሱ ሆኖ ግብሩን የመክፈል ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

2.6. ከውጭ ሀገር የቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ

 በኢ/ያ ነዋሪ የሆነ ግብር ከፋይ በውጭ አገር ባገኘው የኪራይ

ገቢ ግብር ይከፍላል፤

 የተጣራ የውጭ አገር ኪራይ ገቢ ማለት ከተገኘው ኪራይ ጠቅላላ ገቢ ላይ ተቀናሽ ወጪዎች ከተቀነሰ በኃላ ያለው ነው፤

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

2.7. የቤት ኪራይ ኪሣራዎች

 አንድ ቤት አከራይ ለአንድ የግብር አመት የደረሰበትን ኪሳራ ኪሳራው ተካክሶ እስከሚያቅ ድረስ ለ 5 አመታት ኪሳራውን ማሸጋገር ይችላል
 አንድ አከራይ በግብር ከፋይነት ዘመኑ ኪሳራን ማሸጋገር የሚችለው ሁለት ጊዜ ብቻ ይሆናል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

2.8. የሚከራይ አዲስ ቤትን ስለማሳወቅ

• የሚሰራው ቤት እንደተጠናቀቀ ወይም ተከራይቶ ከሆነ ስራ ተቋራጩ እና የቤቱ ባለቤት ከቤቱ ኪራይ በሚገኘው ገቢ ላይ ግብር መክፈል ያለበትን ሰው አድራሻ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለቀቤ/ለከተማ አስተዳደሩ ማስታወቅ አለባቸው፡፡ መረጃው የደረሰው አካልም ለባለስልጣኑ መግለጽ አለበት፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

2.9. የኪራያ ገቢ ግምት አወሳሰን
 የኪራይ ገቢ ግብር በግምት የሚወሰነው የሚከተሉትን መስፈርቶች መሰረት

በማድረግነው

• ውልን መሰረት በማድረግ፣
• ወቅታዊ መራጃ /ገበያ ዋጋን፤የአካባቢን መረጃ፣ በኣካል የገበያን ሁኔታ

በማጥናት፣

• የተደረሰበት ገቢ ለተ .እ.ታ.(VAT) እና ለ ተ .ኦ.ታ.(TOT) መሰረት ሊወሰድ ይችላል፣
• ለደረጃ “ ” ሀ እና “ ”ለ በግምት ግብር አወሳሰን የጠቅላላው ኪራይ ገቢ 35% እንደ ወጪ ተይዞ 65% ግብር የሚከፈልበት ገቢ መሰረት ይሆናል፣

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

የሙከራ ጥያቄ

• ወ/ሮ ትሁን ባንተ የተባለች ግለሰብ አንድ የንግድ ማእከል ተከራይታ የምታከራይ ስትሆን ከምታከራየው አጠቃላይ የአመት ገቢዋ 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) ገቢ ታገኛለች፡፡ ለአንድ ዓመት ለዋና አከራዩ የምትከፍለው 300,000 (ሶስት መቶ ሺ) ነው፡፡ አከራይዋ ገቢውን ለማግኘት ቤቱን ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) ለፓርቲሽን 20,000 ደግሞ ለማስዋቢያ አውጥታለች፡፡
ጥያቄ
1. ግብር የሚከፈልበት ገቢ አስሉ
2. በዚህ ኪራይ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ይሰበሰባል ወይስ አይሰበሰብም ለምን ተርን ኦቨር ታክስስ?

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ክፍል ሦስት

3. የንግድ ስራ ገቢ ግብር (ሰንጠረዥ ሐ)

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3. የንግድ ስራ ገቢ ግብር (ሰንጠረዥ ሐ)

3.1. ግብር የሚከፈልበት የንግድ ስራ ገቢ
• ግብር የሚከፈልበት የንግድ ስራ ገቢ የሚባለው በግብር ዓመቱ ከተገኘው ጠቅላላ የንግድ ስራ ገቢ ላይ በህግ የተፈቀዱ ወጪዎች ተቀንሰው የሚገኘው የተጣራ የገቢ መጠን ነው፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.1. ግብር የሚከፈልበት የንግድ ስራ ገቢ

 ግብር የሚከፍልበት የንግድ ስራ ገቢ የሚወሰነው በአለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች (IFRS) መሠረት በሚዘጋጀው የትርፍና ኪሳራ ወይም የገቢ መግለጫ ላይ በመመስረት ይሆናል፡፡
o ሆኖም ግን ፡ -

•የገቢ ግብር አዋጅ ድንጋጌዎች ፣
•የገቢ ግብር ደንብ፣ እና
•የገንዘብ ሚኒስቴር የሚያወጣቸው መመሪያዎች እንደተጠበቁ

ይሆናሉ፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.2. የንግድ ስራ ገቢ

 ግብር ከፋዩ ዕቃዎችን በማስተላለፍ እና አገልግሎቶችን በመስጠት (መቀጠርን ሳይጨምር) የሚያገኘውን የገንዘብ መጠን ጨምሮ በግብር ዓመቱ ከንግድ ስራ ያገኘው ጠቅላላ የገንዘብ መጠን፣

 የንግድ ስራ ሃብትን በማስተላለፍ የሚገኝ የገንዘብ መጠን
 የግብር ከፋዩ ገቢ ተደርገው የተወሰዱ ሌሎች ማናቸውም ገቢዎች፣  የካፒታል ንብረት የሆነን የንግድ ስራ ሃብት በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.3. የንግድ ስራ ገቢ ግብር

ማስከፈያ መጣኔ

 በድርጅቶች የሚከፈለው የንግድ ስራ ገቢ ግብር መጣኔ 30 (ሰላሳ በመቶ) ነው፡፡
 የግለሰቦች ግብር ማስከፈያ መጣኔዎች በሠንጠረዥ 2 መሰረት ከ10 እስከ 35 በመቶ መጣኔ ግብር ይከፍላሉ

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.3.1.የግለሰቦች ግብር ማስከፈያ መጣኔዎች
ግብር የሚከፈልበት የኪራይ ገቢ በዓመት የኪራይ ገቢ ግብር
መጣኔ

ተቀናሽ

0 7,200 0% 0 7,201 19,800 10% 720
19,801 38,400 15% 1,710
38,401 63,000 20% 3,630
63,001 93,600 25% 6,780
93,601 130,800 30% 11,460
130,801 በላይ 35% 18,000
ሠንጠረዥ 2 የግለሰቦች የንግድ ግበር ማስከፈያ መጣኔ

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.4. ተቀናሽ የሚደረጉ ወጪዎች

 ገደቦች እንደተጠበቁ ሆኖ በንግድ ስራ ገቢው ውስጥ የተካተቱትን ገቢዎች ለማግኘት፣ ለንግዱ ስራ ዋስትና ለመስጠትና የንግድ ስራውን ለማስቀጠል በግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ የተደረጉ አስፈላጊ የሆኑ

ወጪዎች፣
 በግብር ዓመቱ ለተሸጠ የንግድ ዕቃ (trading stock) የወጣ ወጪ፣

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ተቀናሽ የሚደረጉ …
በንግድ ስራው ላይ ሲውሉ ዋጋቸው የሚቀንስ የንግድ ስራ ሃብቶችና ግዙፋዊ ህልወት ለሌላቸው የንግድ ስራ ሃብቶች በግብር ዓመቱ የሚታሰበው ጠቅላላ የእርጅና ቅናሽ፣
የንግድ ዕቃን ሳይጨምር ግብር ከፋዩ በዓመቱ ውስጥ የንግድ ስራ ሃብትን በማስተላለፍ የገጠመው ኪሣራ፡፡
በሠራተኛው የጤና ዕቅድ መሰረት ቀጣሪ በተቀጣሪ ስም የሚከፍለውን የጤና መድን አርቦን ጨምሮ ለሠራተኛው የሕክምና አገልግሎት የሚያወጣው ወጪ
ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.4.1 ዝርዝር ተቀናሽ ወጪዎች

• ግብር ከፋዩ ለንግድ ድርጅቱ እና መኖሪያ ቤት በአንድ የመብራት የስልክ

ወይም የውሃ ቆጣሪ የሚጠቀም በሚሆንበት ጊዜ የመብራት፣ ስልክ እና የውሃ ወጪ በወጪ ተቀናሽ የሚያዘው ከወጪው 75 በመቶ ብቻ ይሆናል፡፡

• አንድ ግብር ከፋይ የንግድ ስራ እንቅስቃሴው በተቋረጠበት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ወይም ስራ ባላገኘበት ጊዜ ያወጣው ወጪ ለምሳሌ (የቤት ኪራይ ፣የሰራተኛ ደመወዝ፣ መብራት፣ውሃ፣ስልክ፣የመሳሰሉት ወጪዎች ሊሆኑ ይችላሉ)

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ዝርዝር ተቀናሽ…

 ግለሰብ የንግድ ስራ ባለሀብት ከመደበኛ የሥራ ቦታው ከ25 ኪሎ ሜትር በላይ በመሄድ የንግድ ስራውን ለማከናወን በሚያደርገው እንቅስቃሴ ለሚያወጣቸው ወጪዎች ለምግብ እና ለመኝታ ለአንድ ቀን እስከ 1000 ብር ይፈቀድለታል በተጨማሪም

 ለትራንስፖርት ያወጣው ወጪ በስራ ላይ ባለው የአየር፣ የውሃ እና የየብስ ትራንስፖርት አገልግሎት ዋጋ መሰረት በማስረጃ ተረጋግጦ የወጪ ተቀናሽ የሚፈቀድለት ሆኖ ከዚህ መጠን በላይ የሚያወጣው ወጪ በተቀናሽ ወጪ አይያዝም፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ዝርዝር ተቀናሽ…

 “የውክልና ወጪ ”(ሪፕረዘንቴሽን ኤክስፔንዲቸር)” 10 በመቶ
 በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ ላለው በቋሚነት ለሚሰራ ድርጅቱ ጥቅም ያደረገውን ትክክለኛ ወጪ
 ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅት በስራ ላይ ላሰማራው አባሉ የሚከፍለው ደመወዝ እንደ ወጪ ተቀናሽ ይፈቀድለታል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ዝርዝር ተቀናሽ…

 በዲዛይን ለውጥ ምክንያት ህንጻ ፈርሶ ሲገነባ የፈረሰው ህንፃ የመዝገብ ዋጋ በውጪ ተቀናሽ ይያዛል፡፡
 የተሸከርካሪ ጎማ የሚሰጠው አገልግሎት ከአንድ ዓመት ያነሰ እንደሆነ እንደ አላቂ ዕቃ ተቆጥሮ በተቀናሽ ወጪ የሚያዝ ይሆናል፡፡
 በካፒታል ዕቃዎች ኪራይ ውል መሰረት ለተያዘ የንግድ ስራ ሀብት የሚፈቀድ ተቀናሽ

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.4.2. የወለድ ወጪ…
 ብድሩ የንግድ ስራ ገቢን ለማግኘት ከዋለ፣ ወይም የወለድ ወጪ በብድሩ የተገኘው ገንዘብ ለንግድ ስራ እንቅስቃሴ መዋሉ ሲረጋገጥ ነው፡፡

 ብድሩ የተገኘው የብሄራዊ ባንክ እውቅና ከሰጠው የፋይናንስ ተቋም ወይም ብድር እንዲሰጥ ከተፈቀደለት የውጭ አገር ባንክ ከሆነ

• ከተፈቀደለት ባንክ ለተወሰደ ብድር የተከፈለ ወለድ ያለገደብ ይቀነሳል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

የወለድ ወጪ..
ብድሩ የተገኘው የብሄራዊ ባንክ እውቅና ከሰጠው የፋይናንስ ተቋም ወይም ብድር እንዲሰጥ ከተፈቀደለት የውጭ አገር ባንክ ውጪ ከሆነ •ለውጭ ሀገር አበዳሪ የተከፈለ ወለድ ተቀናሽ ሊደረግ የሚችለው አበዳሪው ብድር ለመስጠት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ያገኘበትን ሰነድ ቅጂ ለባለሥልጣኑ ካቀረበ ብቻ ነው፡፡
የብድር ወለድ መክፈል የሚቻለው በብሄራዊ ባንክና በንግድ ባንክ መካከል በተደረገ ብድር ከሚታሰብ የወለድ ምጣኔ ከ 2% ባልበለጠ ነው ፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

የወለድ ወጪ…

 አንድ ግብር ከፋይ በዱቤ ለሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት ዋጋውን እስኪከፍል ድረስ ወለድ እንደሚከፈልበት ውል የገባ እንደሆነ ለከፈለው የወለድ መጠን የወጪ ተቀናሽ ይፈቀድለታል፡፡

 የፋይናንስ ተቋማትን ሳይጨምር አንድ ግብር ከፋይ ለተወሰነ የስራ እንቅስቃሴ የወሰደውን ብድር ለሌላ ዓላማ የሚያውል ከሆነ የሚፈቀድለት የወለድ ወጪ ለሌላ አላማ ያዋለው ከተቀነሰ በ ኋላ ነው፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

የወለድ ወጪ…

 ግብር ከፋይ ህንጻ ለመገንባት ብድር የወሰደ እንደሆነ ህንፃው እስኪጠናቀቅ ድረስ የተከፈለው ወለድ በእርጅና ተቀናሽ የሚካተት ሆኖ ህንጻው ተገንብቶ ከተጠናቀቀ በኋላ የተከፈለው ወለድ በወጪ ተቀናሽ የሚፈቀድ ይሆናል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.4.3.ለበጎ አድራጎት ዓላማ የተደረገ

ስጦታ፣

ግብር ከሚከፈልበት ገቢው ላይ 10
በመቶ

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.4.4.የተፈቀዱ የእርጅና ቅናሽ

 ግብር ከፋዩ ገቢውን ለማስገኘት በግብር ዓመቱ ጥቅም ላይ ላዋላቸው ዋጋቸው ለሚቀንስ ሀብቶች እና ግዙፋዊ ሀልዎት ለሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች ዋጋቸው በቀነሰው የገንዘብ መጠን ልክ የእርጅና ቅናሽ ለማድረግ ይፈቀድለታል፡፡ ከርጀና ቅናሽ ጋር ተያይዞ፡-

• “ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሃብቶች ”
• “ዋጋው የሚቀንስ ሀብት የሚሉትን ማወቅ ተገቢ ነው ”

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.4.4.1.ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ማለት ”

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.4.4.1.ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ማለት ”

 ከአንድ ዓመት የሚበልጥ የአገልግሎት ዘመን ያለው፤ (ዋጋቸዉ ከ2000 ብር በላይ ከሆነ)
 በእርጅና ወይም ጊዜው በማለፉ ምክንያት ዋጋው ሊቀንስ የሚችል፤  በከፊል ወይም በሙሉ የንግድ ሥራ ገቢ ለማግኘት ጥቅም ላይ የዋለ፤ግዙፋዊ ሀልዎት ያለው የሚንቀሳቀስ ሀብት ወይም በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ ነው፡ -

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.4.4.2.የንግድ ሥራ ሀብት ማስተላለፍ፡-  አስተላላፊው ሙሉ የእርጅና ቅናሽ ያገኘበትን የንግድ ሥራ ሀብት ግንኙነት ላለው ሰው አስተላልፎ እንደሆነ የተላለፈለት ሰው የእርጅና ቅናሽ ማግኘት አይችልም፡፡
• ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የተላለፈው ሀብት የእርጅና ቅናሽ ጊዜውን ያልጨረሰ ከሆነና የተላለፈበት ዋጋ ከቀሪ የመዝገብ ዋጋው የበለጠ እንደሆነ የእርጅና ቅናሽ ለማስላት መሰረት የሚሆነው ቀሪ የመዝገብ ዋጋው ነው፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.4.4.3.የእርጅና ቅናሽ ስሌት ዘዴዎች

 ግብር ከፋዩ ዋጋቸው ለሚቀንስ ሀብቶች ሁሉ መጠቀም ያለበት አንድ ዓይነት የእርጅና ቅናሽ ዘዴ ነው፡፡
• ሁለት አይነት የዕርጅና ቅናሽ ዘዴዎች ያሉ ሲሆን
• ቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ እና
• ዋጋው እየቀነሰ የሚሄድ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ በመባል ይታወቃሉ፡፡ https://www.youtube.com/watch?v=_pas1ETbrj8

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.4.4.4.ቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ

 በቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ ብቻ መሰላት ያለባቸው
• ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች፣
• በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ፤
• ማንኛውም “ ” ግብር ከፋይ አስተላላፊ ተብሎ ከሚጠራ ግንኙነት ያለው ሰው ላገኘው እና በአስተላላፊው ሙሉ የእርጅና ቅናሽ ላገኘበት ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ወይም ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት የእርጅና ቅናሽ ማግኘት አይችልም ፡፡
ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.4.4.5.ምሳሌ

 አሴቱ(ሃብቱ) 1ሚሊዮን ብር ዋጋ ያለው ሲሁን የመጠቀሚያ ጊዜው ለ5 አመታት ነው ይህ ሃብት በአመት 20 በመቶ ድፕሪሼት(Depreciate) ያደርጋል ተብሎ ቢታሰብ በአመስት አመቱ መጨረሻ ላይ የ አሴቱ (ሃብቱ) ዋጋ ምንያህል ይሆናል? በቀጥተኛ የዕርጅና ቅናሽ ዘዴ አስሉ

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.4.4.6.መልስ

አመት የአሴቱ የመጀመሪያ
የመዝገብ ዋጋ

(የሃብቱ ዋጋ)

የሚቀንሰው የዋጋ

መጠን (depreciation
rate)

የመጨረሻው የመዝገብ ዋጋ

1 1000,0000 200,000 800,000

2 800,000 200,000 600,000

3 600,000 200,000 400,000

4 400,000 200,000 200,000

5 200,000 200,000 200,000

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.4.4.7.ዋጋው እየቀነስ የሚሄድ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ

 ለአንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት ዋጋው ለሚቀንስ ሀብት የተፈቀደው ዋጋው እየቀነሰ በሚሄድ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ መሠረት የሚወሰን የእርጅና ቅናሽ መጣኔ በዓመቱ መጀመሪያ ባለው የሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ላይ ተፈጻሚ በማድረግ ይሰላል፡፡

 የግብር ከፋዩ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ቀሪ ዋጋ ከብር ሁለት ሺህ የማይበልጥ ከሆነ በአንድ ጊዜ በወጪነት ይያዛል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.5.የእርጅና ቅናሽ መጣኔዎች
 ዋጋው በሚቀንስ ሀብት ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ የእርጅና ቅናሽ መጣኔዎች

ዋጋው የሚቀንስ ሀብት

የቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ
መጣኔ

ዋጋው እየቀነሰ የሚሄድ የእርጅ
ናቅናሽ ዘዴ መጣኔ

ኮምፒውተር፣ሶፍትዌር እና የመረጃ ማከማቻ መሣሪያ 20 በመቶ 25 በመቶ

ግሪን ሃውስ 10 በመቶ -

ግሪንሃውስንሳይጨምር በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ
የሚደረግ ማሻሻያ

5 በመቶ -

ሌላ ማንኛውም ዋጋው የሚቀንስ ሀብት 15 በመቶ 20 በመቶ

ለማዕድንና ነዳጅ የልማት ሥራዎች ጥቅም ላይ የሚውል
ዋጋው የሚቀንስ ሀብት

• በመቶ 30. በመቶ

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.5.1.ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች መጣኔ
 ሀ. የንግድ ስራ ከመጀመሩ በፊት የተደረገ ወጪ ሃያ አምስት 25 %

በመቶ፣

 ለ) በፊደል ተራ (ሀ) ከተመለከተው ውጪ ለሆነ ከአስር ዓመት በላይ ለሚያገለግል ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት አስር 10 % በመቶ፣ ወይም

 ሐ) ለሌላ ማንኛውም ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት መቶ በመቶ(100%)
 ግዙፋዊ ሀልዎት ለሌለው ሀብት የአግልገሎት ዘመን በማካፈል የሚገኘው መጣኔ፣ይሆናል (በከፊል ለንግድ ስራ ለዋለ ሃብት)
ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.5.2.ማሻሻያዎች ላይ የእርጅና ቅናሽ
ጥገናዎችና ማሻሻያዎች ላይ የሚደረግ የወጪ ተቀናሽ
• ማንኛውም ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት ዋጋው በሚቀንስ ሀብት ላይ ላደረገው የጥገና ወይም ማሻሻያ ወጪ በግብር ዓመቱ የወጪ ተቀናሽ ይፈቀድለታል፡፡

• የሚፈቀደው የወጪ ተቀናሽ ሀብቱ በግብር ዓመቱ መጨረሻ ካለው የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ሃያ በመቶ (20 %) ፣ ሊበልጥ አይችልም፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.5.3.ዝርዝር ስለ የዕርጅና ቅናሽ

 በግብር ከፋዩ የተገነባ ለንግድ ስራ ጥቅም ላይ የዋለው የህንፃ ክፍል የእርጅና ቅናሽ መታሰብ የሚጀምረው ሀብቱ የንግድ ስራ ገቢውን ለማስገኘት ለአገልግሎት ዝግጁ ከሆነበት እና አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ቀን አንስቶ ሲሆን ተቆጣጣሪው ባለስልጣን ለግብር ከፋዩ የህንፃ ግንባታው ስለመጠናቀቁ የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ከሰጠበት ጊዜ በፊት ሊሆን አይችልም፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

የዕርጅና ቅናሽ …

 የአንድ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት የእርጅና ቅናሽ ለማስላት

መሰረት የሆነው የተሰራበት ወይም የተገዛበት ዋጋ የሚገልጽ ሰነድ ታክስ ከፋዩ ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ ባለስልጣኑ የተሰራበት ወይም የተገዛበት የገበያ ዋጋ መሰረት በማረግ 70 በመቶ የእርጅና ተቀናሽ ይፈቀድለታል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.6.የማስታወቂያ ወጪ

 ግብር ከፋይ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለማስተዋወቅ በተለያዩ ዝግጅቶች ላይ የሚያደርገው የማስተዋወቅ ስራ በገንዘብ ወይም በምርት ወይም በአገልግሎት የሚፈጽመው ክፍያ በወጪ ተቀናሽ የሚያዘው ከጠቅላላ ገቢው (3% በመቶ) ባልበለጠ መጠን ብቻ ነው፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

የማስታወቂያ ወጪ…

 ለመገናኛ ብዙሀን ወይም ለማስታወቂያ ድርጅት የሚከፍለው ክፍያ ሙሉ በሙሉ በወጪ ተቀናሽነት ይያዛል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.7.የምርት ብክነት ወጪ

በምርት ዝግጅትና አቅርቦት ሂደት በብጣሪ፣ ሰሊጥ ኑግ በትነት፣ ነዳጅ በማቅለጥ፣ በሽርፍራፊ፣ ቡና በቆይታ ጊዜ ወዘተ) የሚባክን ምርት የዕቃ መጠን በሚመለከተው የመንግስት አካል በቀረበ ጥናት መሰረት እንደ ወጪ ሊያዝ ይችላል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.8.የመዝናኛ ወጪ

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

የመዝናኛ ወጪ …

 የማዕድን ማውጣት እና ፍለጋ፤ የማኑፋክቸሪንግና የግብርናና

ሆርቲ ካልቸር ስራ ላይ የተሰማራ ቀጣሪ ለተቀጣሪው በነፃ የሚያቀርበው ምግብ እና መጠጥ ዋጋ በወጪ የሚያዘው በአንድ ወር የሚያወጣው ወጪ በወሩ ለተቀጣሪዎቹ ካወጣው አጠቃላይ የደሞዝ ወጪ ከ 30% ባልበለጠ መጠን ብቻ ነው፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

የመዝናኛ ወጪ …

 ሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶች ወይም ሌሎች የምግብ አገልግሎት የሚያቀርቡ ተቋማት ውስጥ ለተሰማሩ ሰራተኞች ለተቀጣሪዎች የሚያቀርቡት የምግብ እና መጠጥ ወጪ ተቀናሽ የሚያደርገው በአንድ ወር የወጣው ወጪ በወሩ ለተቀጣሪዎቹ ከወጣው አጠቃላይ የደሞዝ ወጪ 20% ያልበለጠ መጠን ብቻ ነው፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.9.የማይሰበሰብ ዕዳ በወጪነት ስለመያዝ
 ዕዳው ቀደም ሲል የንግድ ስራ ገቢ ሆኖ ተይዞ /ተመዝግቦ/ ከሆነ፣
 ዕዳውን ለማስከፈል አስፈላጊ የህግ እርምጃ ተወስዶ ማስመለስ

ያልተቻለ እንደሆነ ነው፣

 ዕዳው ከግብር ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ የተሰረዘ እንደሆነ፣ እና
 የሚቀነሰው የዕዳ መጠን ከግብር ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ ከተሰረዘው የዕዳ መጠን መብለጥ የለበትም፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.9. ኪሳራ
 ኪሳራ ለማሸጋገር የሚቻለው ኪሳረው ከደረሰበት ዓመት ቀጥሎ

ላሉት አምስትዓመታት ነው፡

 ኪሳራ ለማሸጋገርና በወጪነት ለመያዝ የሚፈቀደውም ለሁለት የግብር አመታት ብቻ የደረሰ ኪሳራ ነው፡፡

 አንድ ግብር ከፋይ የሚሸጋገር ኪሳራ ከአንድ የግብር ዓመት በላይ ያጋጠመው ከሆነ ግብር ከፋዩ መጀመሪያ የገጠመው ኪሣራ በቅድሚያ ይቀነስለታል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.9.1.ባንኮች እና የመድን ኩባንያዎች ኪሣራ መጠባበቂያ

 ማንኛውም ባንክ በአንድ የግብር ዓመት ለኪሣራ የያዘው

የመጠባበቂያ ሂሣብ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለመጠባበቂያ ሂሣብ በተቀመጠ የጥንቃቄ መሥፈርት መሠረት እስከተሰላ እና ከፋይናንስ

ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች ጋር የተጣጣመ እስከሆነ ድረስ በግብር ዓመቱ የመጠባበቂያ ሂሣቡ መጠን ሰማንያ (80) በመቶ በተቀናሽ ወጪ ይያዝለታል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ባንኮች እና የመድን ኩባንያዎች ኪሣራ መጠባበቂያ

 ጠቅላላ መድን በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ የመድን ኩባንያ በአንድ

የግብር ዓመት ጊዜው ላላለፈ ሥጋት የያዘው የመጠባበቂያ ሂሣብ መጠን በሂሣብ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት የተሰላ እስከሆነ ድረስ በዓመቱ መጨረሻ ላይ የሚታየው ቀሪ የመጠባበቂያ ሂሣብ ለግብር ዓመቱ በተቀናሽ ወጪ ይያዝለታል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.9.2.የህይወት መድን ንግድ ሥራ ግብር የሚከፈልበት ገቢ

 የህይወት መድን በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ የመድን ኩባንያ የአንድ ግብር ዓመት ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚከተለው ቀመር መሠረት ይሰላል፡፡ (ሀ+ለ+ሐ+መ) – (ሠ+ረ+ሰ+ሸ) ለዚህ ቀመር አፈፃፀም፡-

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

3.10.ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች እና ኪሳራዎች
• የካፒታልነት ባህርይ ያላቸው ወጪዎች፤
• የኩባንያ አክሲዮን ወይም የሽርክና ማህበር መሠረት የሆነውን ካፒታል ለማሳደግ የሚወጣ ወጪ፤

• ከተቀጣሪው የወር ደመወዝ 15% (አሥራ አምስት መቶኛ) በላይ በፈቃደኝነት የሚደረግ የጡረታወይም የፕሮቪደንት ፈንድ መዋጮ፤
• የአክሲዮን ድርሻ እና የትርፍ ድርሻ ክፍፍል፤ በመድን፣ በካሳ ወይም በዋስትና ውል መሠረት የተመለሰ ወይም ሊመለስ የሚችል ወጪ ወይም ኪሳራ፤

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ተቀናሽ የማይደረጉ …

 ማንኛውንም ሕግ ወይም ውል በመጣስ የሚጣል የገንዘብ ቅጣት ወይም የሚከፈል ካሳ፤

 ግብር ከፋዩ በሂሳብ መዝገቡ የሚይዘው በወቅቱ ወጪ ያልተደረገ ነገር ግን ለወደፊት በግብር ዓመቱ ለሚከሰቱ ወጪዎች ወይም ኪሳራዎች መጠባበቂያ ይሆን ዘንድ የሚያዝ ገንዘብ ወይም የመጠባበቂያ ሂሣብ፤

 ግብር ከፋዩ ለራሱ የሚያወጣው የግል ውጪ፤

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ተቀናሽ የማይደረጉ …

 በገቢ ግብር አዋጅ ወይም በውጭ ሀገር የታክስ ሕግ መሠረት የተከፈለ

የገቢ ግብር ወይም ተመላሽ የሚደረግ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤

 መሥሪያ ቤቱን ወክሎ በተለያዩ ቦታዎች ለሚገኝ ተቀጣሪ ከተቀጣሪው ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ 10 % (አሥር በመቶ) በላይ የሚከፈል የኃላፊነት አበል፤

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ተቀናሽ የማይደረጉ …

 ከሚከተሉት በስተቀር ለመዝናኛ የሚወጣ ወጪ ፤

1. የግብር ከፋዩ የንግድ ሥራ የመዝናኛ አገልግሎት መስጠት ሲሆን፤ወይም
2. ተቀናሽ እንዲደረግ በሚፈቅደው ልክ በማዕድን ማውጣት፣ በማኑፋክቸሪንግ ወይም በግብርና ሥራ የተሠማራ ቀጣሪ ሠራተኞቹን ለማዝናናት የሚያወጣው ወጪ፤

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ተቀናሽ የማይደረጉ …

 ለበጎ አድራጎት ከሚሰጥ ስጦታ ውጭ የሚደረግ ስጦታ ወይም እርዳታ፤

 ግብር ከፋዩ አንድን የንግድ ሥራ ሀብት ግንኙነት ላለው ሰው ሲያስተላልፍ የሚደርስ ኪሳራ፤

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

የሙከራ ጥያቄዎች
•1ኛ. ስንት አይነት የዕርጅና ቅናሽ ዘዴዎች አሉ ? ዘርዝሩ
•2ኛ. አሴቱ(ሃብቱ) 1.5 ሚሊዮን ብር ዋጋ ያለው ሲሁን የመጠቀሚያ ጊዜው ለ5 አመታት ነው ይህ ሃብት በአመት 10 በመቶ ድፕሪሼት(Depreciate) ያደርጋል ተብሎ ቢታሰብ በአምስት አመቱ መጨረሻ ላይ የ አሴቱ (ሃብቱ) ዋጋ ምንያህል ይሆናል ? በቀጥተኛ የዕርጅና ቅናሽ ዘዴ አስሉ
• 3ኛ. ሙሉ ለሙሉ ተቀናሽ የሚደረጉ እና በገደብ ተቀናሽ የሚደረጉ የንግድ ስራ ወጪዎችን ዘርዝሩ

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

የሙከራ…

• 4ኛ. የማይሰበሰብ እዳ በተቀናሽነት ሊያዝ የሚችለው ምን፤ምን መስፈርቶች ሲሟሉ ነው ?
• 5ኛ፣ በአንድ የግር ዘመን ኪሳራ የገጠመው ሰው ኪሳራውን የሚያሸጋግረው ለስንት አመታት ነው ?

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ምዕራፍ አራት
4. የሂሳብ መዝገብ አያያዝ እና የሂሳብ ዓመት

https://www.youtube.com/watch?v=NquuY41FrrA

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

4. የሂሳብ መዝገብ አያያዝ እና የሂሳብ ዓመት
የራሱን የሂሳብ አመት እንደ ግብር አመት እንዲጠቀም ፈቃድ ለተሰጠው ግለሰብና ድርጅት የሂሳብ ዓመት ነው የሚባለው የግብር ከፋዩ ዓመታዊ የፋይናንስ ሂሳብ

ሚዛን(Balancesheet) በሚዘጋበት ጊዜ የሚጠናቀቀው የአስራ ሁለት ወራት ጊዜ ነው፡፡

• https://www.youtube.com/watch?v=xlXDZyZ9 azk

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

4.1. የካፒታል ሀብት ሲተላለፍ የሚያዝ መረጃ

• የተላለፈው የካፒታል ሀብት የተገኘበትን ቀን፤ የተገኘበትን ዋጋ ፣
• ሀብቱን ለማሻሻል የወጣ ማንኛውም ወጪ እና
• ሀብቱ በሚተላለፍበት ጊዜ ለግብር ከፋዩ የተከፈለ የማስተላለፊያ ዋጋ አጠቃሎ የሚይዝ የሂሳብ መዝገብ መያዝ አለበት፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

4.2. ታክስ ከፋዩ መያዝ ያለበት

ሰነድ ዓይነት

 ማንኛውም የደረጃ “ሀ” እና የደረጃ “ለ” ግብር ከፋይ በግብር ከፋይነት

ለተመዘገበበት እና የንግድ ፈቃድ ላወጣበት ለእያንዳንዱ የንግድ መስክ ያዋለውን ሀብት እና ኢንቨስትመንት እንዲሁም በእያንዳንዱ ዘርፍ ከተደረገው የንግድ እንቅስቃሴ የተገኘውን ትርፍና ወይም ኪሣራ በትክክል የሚያሳይ በሀርድ ኮፒና ወይም በሶፍት ኮፒ ተደራጅቶ የተያዘ ሰነድ መያዝ አለበት፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

መያዝ ያለበት ሰነድ…

 ግብር ከፋዩ ያለውን የንግድ ሥራ ሀብት(Fixed Assets) እንደ ዓይነቱ እና

እንደ አገልግሎቱ በመለየት የሚመዘግብበት የንግድ ሥራ ሀብት መዝገብ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን የዚህ ዓይነት መዝገብ፡

 እያንዳንዱ የንግድ ሥራ ሀብት የተገዛበት ወይም የተገኘበት ቀን እና ዋጋ፣
 የንግድ ሥራ ሀብቱን ለማሻሻል የተደረገ ማንኛውም ከሀያ በመቶ በላይ የሆነ ወጪ፤

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

መያዝ ያለበት ሰነድ…  በዓመቱ መጨረሻ የንግድ ሥራ ሀብቱ ያለውን የተጣራ የመዝገብ ዋጋ  የእያንዳንዱ የተጠራቀመ የእርጅና ቅናሽ መጠን የሚያሳይ መሆን

አለበት፡፡

 ኢንቨስትመንት የሚያካሂድ ግብር ከፋይ የኢንቨስትመንት ሥራው ተጠናቆ የኢንቨስትመንቱ አጠቃላይ ካፒታል እስኪታወቅ ድረስ በየጊዜው የሚያወጣው ወጪ የሚመዘገብበት ራሱን የቻለ መዝገብ (ledger) ሊኖረው ይገባል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን



መያዝ ያለበት ሰነድ…

ማንኛውም ግብር ከፋይ
ብድር በሚወስድበት ጊዜ

የብድር
ወይም
የዱቤ
ሽያጭ
ስምምነ
ት፣

የዕዳ አከፋፈል ሁኔታ

(Mode of payment)፣

የአበዳሪው
ዕቃ/
አገልግሎ
ት በዱቤ
የሸጠው
ሰው ሙሉ
መረጃ፣

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

መያዝ ያለበት ሰነድ…
 የድርጅቱን ካፒታል መዝገብን በተመለከተ
• ካፒታሉ የግል ወይም በአክስዮን መዋጮ የተገኘ መሆኑን የሚያሳይ

ሰነድ፣

•በአክሲዮን ድርሻ የተያዘው የካፒታል መጠን፣
• የተከፈለ እና ያልተከፈለ የካፒታል መጠን፣
•ያልተካፈፈለ የትርፍ መጠን፣
•ለካፒታል ማሳደጊያ የዋለ የትርፍ መጠን፣
ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን • የተከፋፈለ የትርፍ ድርሻ መጠን

መያዝ ያለበት ሰነድ…

የሒሳብ መግለጫ ይዘቶች
•የሀብት እና የዕዳ መግለጫ (balance sheet) ፣
• የጥሬ ገንዘብ ገቢ እና ወጪ መግለጫ (Cash flow statement)
• የድርጅቱ የካፒታል ለውጥ መግለጫ (Change of capital statement) ፣
• የትርፍና ኪሣራ መግለጫ (Profit and loss statement) ፣

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

መያዝ ያለበት ሰነድ…

 አምራች ድርጅት ከሆነ የምርት ሂደት መግለጫ (Production statement) እና
 ለተመረተ ምርት የወጣ የምርት ወጪ መግለጫ (Statement of Cost of Goods Manufactured) እና Stock Inventory

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

መያዝ ያለበት…

 የሂሳብ መዝገብ ለማዘጋጀት ሶፍትዌር መጠቀም •ማንኛውም ግብር ከፋይ የሂሳብ መዝገብ ለማዘጋጀት ሶፍትዌር የሚጠቀም ከሆነ የሶፍትዌሩን ከአጠቃቀም ማንዋል ጋር ለታክስ ባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

•ታክስ ባለስልጣኑ የሂሳብ መዝገብ ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ የሚውል

ሶፍትዌር ሲቀርብለት ሶፍትዌሩ ለታክስ አስተዳደሩ አመቺ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

መያዝ ያለበት ሰነድ…

የግብር ከፋዩ ወጭ ተቀባይነት ስያጣ ማስተካኪያዎች
• ለቋሚ የንግድ ስራ ሀብት፣ ዕቃው በተሰራበት ወይም በተገዛበት ወቅት የዕቃው የገበያ ዋጋ 70%፣

• ለሌሎች ዕቃዎች ግዢ፣ የዕቃውን የገበያ ዋጋ 65% በወጪነት በመያዝ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

መያዝ ያለበት ሰነድ…

 ሰነድ በሚመለከተው አካል ስለማስመዘገብ
•ለንግድ ዓላማ የሚውል የቤት ኪራይ፣ የመጋዘን ኪራይ፤የጥናት አገልግሎት ግዢ፣ማንኛውም አይነት የማሽነሪ ኪራይ፣የንግድ ተሸከርካሪ ኪራይ፣

•ይሁን አንጂ ሶስት ወር እና ከሶስት ወር በላይ የቆየ ወይም የሚቆይ

የኪራይ ወይም የጥናት አገልግሎት ውል ስምምነት ያልተመዘገበ መሆኑ ከተረጋገጠ ሰነዱ ውድቅ ተደርጎ ወጪው በግምት ይወሰናል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

መያዝ ያለበት ሰነድ…

 የሂሳብ መዝገብ አዘገጃጀት
• የሂደሳብ መዝገብ በባለሞያዎች መዘጋጀት አለበት
• ግብር ከፋዩ ሞያዊ ብቃት ያለው ከሆነ ራሱ ማዘጋጀት ይችላል
• የደረጃ “ለ” ግብር ከፋይ እና በፈቃደኝነት የሂሳብ መዝገብ የሚይዝ የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋይ ቀለል ያለ የሂሳብ ዘዴ በመጠቀም የሂሳብ መዝገብ መያዝ ይችላሉ፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

መያዝ ያለበት ሰነድ…

ቀለል ያለ የሂሳብ አያያዝ ዘዴን ተጠቅሞ የሂሳብ መግለጫ በሚያቀርብበት ጊዜ
• ግብር ከፋዩ አስቀድሞ የተመዘገበውን የቋሚ የንግድ ስራ ሀብት ብዛት፣ ዓይነት እና የመዝገብ ዋጋ የሚያሳይ ሠንጠረዥ፣

• በግብር ዓመቱ ውስጥ የተገዛ እና 100 % የእርጅና ቅናሽ የተደረገለት የንግድ ስራ ሀብት ብዛት፣ ዓይነትና ዋጋ፣

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

4.2.1.ቀለል ያለ የሂሳብ አያያዝ ዘዴን ተጠቅሞ የሂሳብ መግለጫ በሚያቀርብበት ጊዜ

በግብር ዘመኑ የተላለፈ ወይም የተወገደ የንግድ ሥራ ሀብት ብዛት፣ ዓይነት እና ዋጋ የሚገልጽ ደረሰኝና ተያያዥ ማስረጃዎች፤
ለቀጣይ የግብር ዘመን የዞረ ቋሚ ንብረት ብዛት፣ ዓይነት እና ዋጋ የሚያሳይ ሰንጠረዥ፤

ካለፈው የግብር ዘመን ሳይሸጥ የቀረ ንግድ ዕቃ (Stock) ብዛት፣ አይነት እና ዋጋ የሚያሳይ ሰንጠረዥ፣

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

4.2.1.ቀለል ያለ የሂሳብ አያያዝ ዘዴን ተጠቅሞ የሂሳብ መግለጫ በሚያቀርብበት ጊዜ

 ግብር ከፋዩ አምራች ከሆነ በግብር ዘመኑ በምርት ሂደት ላይ ያለና ወይም ጥቅም ላይ ያልዋለ ጥሬ ዕቃ ብዛት፣ አይነት እና ዋጋ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

፣

 በግብር ዓመቱ ውስጥ የተፈፀመ የንግድ ዕቃ ሽያጭ እና ግዢ ዝርዝር ከግብይት ደረሰኝ ጋር፣

 በግብር ዓመቱ ውስጥ ለቤት ኪራይ የተከፈለ ወጪ እና ቤት በማከራየት የተገኘ ገቢ መግለጫ፣ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

4.3.ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ ውሎች

 ንግድ ሥራ ገቢ ግብር ሂሳቡን በተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ዘዴ የሚይዝ ግብር ከፋይ ከተዋዋለው የረዥም ጊዜ ውል ውስጥ በግብር ዓመቱ የተጠናቀቀውን መቶኛ መሠረት በማድረግ ገቢውን በንግድ ሥራ ገቢው ውስጥ ሲያካትት ወጪውም በዚያው መቶኛ ልክ በተቀናሽነት እንዲያዝለት ይደረጋል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ ውሎች …

 ግብር ከፋዩ ለረጅም ጊዜ ከተደረገ ውል ጋር ተያይዞ በውሉ የመጨረሻ ዓመት ኪሳራ የደረሰበት ኪሳራውን እንዲያሸጋግር የተፈቀደለት ቢሆንም ኪሳራውን ማሸጋገር ያልቻለ ሆኖ በውሉ ዘመን መጨረሻ በኢትዮጵያ የንግድ ሥራ መሥራት ያቆመ እንደሆነ ይህ ግብር ከፋይ የደረሰበት ኪሳራ ወደ ኋላ ተመልሶ በአምናው የግብር ዓመት በተቀናሽነት እንዲያዝለት ይደረጋል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

የሙከራ ጥያቄ

• 1ኛ. የካፒታል ሀብት ሲተላለፍ የሚያዝ መረጃ
• 2.ኛ. የሒሳብ መግለጫ ይዘቶችን ዘርዝሩ

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ምዕራፍ አምስት

5. ድርጅትን በመቆጣጠር ረገድ የሚደረግ ለውጥና የኩባንያ እንደገና መደራጀት

አንድን ድርጅት በመቆጣጠር ረገድ የሚደረግ ለውጥ •አንድ ድርጅት የደረሰበትን ኪሣራ ወደ መሸጋገሪያ ዓመት ወይም ወደ ሚቀጥለው ዓመት ማሸጋገር የሚችለው የኩባንያውን ከ 50% በላይ የሆነውን የዋና ባለቤትነት ድርሻ በኪሣራው ዓመት ፣ በመሸጋገሪያው ዓመትና በሁሉም ጣልቃ ገብ ዓመታት የያዘው ተመሳሳይ ሰው የሆነ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

5.1.የኩባንያ እንደገና መደራጀት

 ከሁለት በላይ የሆኑ ነዋሪ ኩባንያዎች መዋሃድ፡፡
 የአዲሱ ድርጅት አባል የሆነ አንድ ድርጅት የሌላውን ድርጅት 50% ልዩ የአክሲዮን ባለቤት ድርሻ ከአዲሱ ድርጅት በሚገኘው የአክሲዮን ለውጥ ብቻ መያዝ፡፡

 እንደገና በሚደራጀው ድርጅት ውስጥ አባል የሆኑ ሁለት ድርጅቶች አንዱ የሌላውን ከ 50% በላይ የሆነ የአክሲዮን ባለቤትነት ድርሻ ልዩ መብት በማያሰጥና የድምጽ ተሳትፎ ብቻ በሚያስገኝ አ ኳኋን መጠቅለል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

5.2.የማዕድንና የነዳጅ ስራዎች ገቢ

ግብር

የማዕድንና ‑ የነዳጅ ስራ ከሌላው የንግድ ስራ ለየት የሚያደርገው፡ የገቢ ምንጩ ሊተካ የማይችል የመንግስት (የሃገር) የተፈጥሮ

ሃብትን በመጠቀም የሚገኝ በመሆኑ፡፡

ስራው ከፍተኛ ስጋት (Risk) ያለበትና ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ

በመሆኑ፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

 የማዕድንና የነዳጅ ስራ ከሌላው የንግድ ስራ ለየት የሚያደርገው

• የማዕድንና የነዳጅ ፈለጋ ስራ ረጅም ጊዜ የሚወስድና

በስተመጨረሻም ውጤት እንደሚገኝ አስቀድሞ እርግጠኛ መሆን

የማይቻልበት ሁኔታ (uncertainity) ያለበት በመሆኑ፡፡
• ንግዱ የመንግስት ልዩ ፈቃድ የሚጠይቅና ልዩ ቁጥጥርና ክትትል የሚደረግበት እንዲሁም የመንግስት ድርሻ ያለበት በመሆኑ፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

5.2.2.ፈቃድ በተሰጠው ሰውና በስራ ተቋራጭ ላይ ግብር
ስለመጣል

 ማዕድን የማውጣት መብት በተሰጠው ባለፈቃድ (ፈቃድ የተሰጠው ሰው) እና ከመንግስት ጋር የነዳጅ ስምምነት ባደረገው ስራ ተቋራጭ ላይ የተጣለው የንግድ ስራ ገቢ ግብር 25% ነው፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ፈቃድ በተሰጠውና በስራ ተቋራጭ ላይ ግብር ስለመጣል…

 ፈቃድ የተሰጠው ሰው በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ንዑስ ስራ ተቋራጭ ከሚፈጽመው ማንኛውም ክፍያ ላይ የሞቢላይዜሽንና የዲሞቢላይዜሽን ወጪዎች ተቀንሰው በሚቀረው መጠን ላይ 10% ግብር ቀንሶ ለባለስልጣኑ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ የነዳጅ ንዑስ ስራ ተቋራጭ ከዚህ ዓይነት ግብር ነጻ ተደርጓል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

5.2.2.ባለፈቃዱ ወይም ስራ ተቋራጩ ተቀናሽ የሚደረግላቸው ወጪ፣
 ኪሳራው ወደሚቀጥለው አመት ይሸጋገራል
 ኪሳራውን ማሸጋገር የሚቻለው ኪሳራው ከደረሰበት አመት ቀጥሎ ላሉት 10 አመታት ነው
 የተደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ ወጪያቸው በተቀናሽ ይያዛል
 የፍለጋ ወጪ፤የማልሚያ ወጪ
 የመልሶ ማቋቋሚያ ወጪ፣
 የኢንቨስትመንት ተቀናሽ(እስከ 5 በመቶ ተቀናሽ ይያዛል

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

5.2.3.የማዕድን ወይም የነዳጅ መብት

ስለማስተላለፍ

 ባለፈቃዱ ወይም ስራ ተቋራጩ መብቱ ከሚተላለፍበት ሰው ጋር “ ” የማስተላለፍ ስምምነት ተብሎ የሚጠቀስ የጹሁፍ ስምምነት ማድረግ አለባቸው፡፡

 መብት አስተላላፊው ከተላለፈው መብት ጋር በተያያዘ ላወጣው ወጪ ያገኘው ተቀናሽ ተመላሽ እንደተደረገ ወጪ ተቆጥሮ በተቀበለበት የግብር ዓመት እንደተገኘ ገቢ ተርጎ ይወሰዳል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

5.2.4.የማዕድን ወይም የነዳጅ መብትን በተዘዋዋሪ መንገድ ስለማስተላለፍ

 የባለፈቃዱ ወይም የስራ ተቋራጩ ድርጅት ዋና ባለቤትነት ከ 10%

በላይ ከተለወጠ ባለፈቃዱ ወይም ስራ ተቋራጩ ለውጡን ለባለስልጣኑ ወዲያወኑ በጹሁፍ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

5.3. ዓለም አቀፍ ግብር

 በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው በውጭ አገር ካገኘው የንግድ ስራ ገቢ

ላይ የውጭ አገር ግብር የከፈለ እንደሆነ በውጭ አገር የከፈለው የንግድ ስራ ገቢ ግብር እንዲካካስለት ይደረጋል፡፡ የሚካካሰው የግብር መጠንም ፡-

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ዓለም አቀፍ ግብር …

 በውጭ አገር ከተከፈለው ገቢ ግብር ፣
 በውጭ አገር በተገኘው ገቢ ላይ በዚህ አዋጅ መሰረት ሊከፈል

ከሚገባው የንግድ ስራ ገቢ ግብር

 ከሁለቱ ከአነስተኛው የበለጠ አይሆንም፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ዓለም አቀፍ ግብር …

 በውጭ አገር የተከፈለ ግብር ሊካካስ የሚችለው፣
• ግብር ከፋዩ ሊከፈል የሚገባውን ግብር ገቢው ከተገኘበት የግብር ዓመት ቀጥሎ ባሉት ሁለት የግብር ዓመታት ወይም ደግሞ ባለስልጣኑ በሚፈቅደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ የከፈለ እንደሆነና

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ዓለም አቀፍ ግብር …

የውጭ አገር የንግድ ስራ ኪሳራዎች
•ግብር ከፋዩ የውጭ አገር ገቢን ለማግኘት ያወጣው ወጪ ተቀናሽ

የሚደረገው በውጭ አገር ካገኘው ገቢ ላይ ብቻ ነው፡፡

•በግብር ዓመቱ በውጭ አገር ያጋጠመውን ኪሳራ ግብር ከፋዩ በሚቀጥለው የግብር ዓመት ከውጭ አገር ባገኘው ገቢ ላይ በማካካስ በሰንጠረዠ ሐ መሰረት ተቀናሽ ይደረግለታል፡፡ “ ” (እስከሚቀጥለው 5 ዓመታት)

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ዓለም አቀፍ ግብር …

 ለኩባንያ ካፒታል የሚወሰድ ብድር (Thin capitalization)
• በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር ያለ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ የግብር ዓመቱ አማካይ ዕዳ ከአማካይ የካፒታል መዋጮው ጋር ሲነጻጸር ከ 2ለ1 ሬሽዮ የበለጠ እንደሆነ ኩባንያው ከዚህ ሬሽዮ በላይ በሆነው ዕዳ የከፈለው ወለድ አይቀነስለትም፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ዓለም አቀፍ ግብር …

ተቀናሽየማይደረገውየወለድመጠን

ሀ

• ሀ)
ኩባንያውበግብርዓመቱተቀናሽእንዲደረግለትየሚጠይቀውየወለድወጪ ፤

• ለ)ኩባንያውከተፈቀደውመጠንበላይየወሰደውብድር፤ እና
• ሐ)ኩባንያውበግብርዓመቱያለበትአማካይዕዳነው፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

5.4.ግብርን በሚመለከት

የሚደረጉስምምነቶች (tax treaties)

 “የግብር ስምምነት ማለት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረትና ታክስ ” ላለመክፈል የሚደረግን የግብር ስወራ (Tax Evasion) ለመከላከል የሚደረግ ዓለም አቀፍ ስምምነት ነው፡፡

 ግብርን የሚመለከቱ ስምምነቶች ከውጭ አገር መንግስት ወይም መንግስታት ጋር የሚደረጉት በገ /ኢ/ት/ሚ/ ነው፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

የግብር ስምምነቶች (tax treaties)…

በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጻሚነት ባለው የግብር ስምምነት የውል ቃላትና በዚህ አዋጅ መካከል አለመጣጣም የተፈጠረ እንደሆነ የስምምነቱ ድንጋጌ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡
ይሁንና አለመጣጣሙ የተፈጠረው ፡-
•በተዋዋይ አገር ነዋሪ ያልሆነ ሰው ከ50% በላይ ባለቤት የሆነበት ድርጅት የታክስ ነጻ መብትን በሚያሰጥና የግብር ማስከፈያ መጣኔ ቅነሳን በሚያስከትል የግብር ስምምነት ተጠቃሚ ሊሆን እንደማይችል ፣

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

5.5.የገንዘብ ምንዛሬ

• ግብር ከፋዮች በወጭ ምንዛሪ የተፈጸመ ክፍያ ወይም የተደረገ ግብይት ሲኖራቸው የገንዘቡን መጠን (ወጪም ሆነ ገቢ) በብር መግለጽ አለባቸው፡፡

• የገንዘቡ መጠን በውጭ ምንዛሪ የተያዘ ከሆነ ገንዘቡ በሂሳብ መዝገብ በሚመዘገብበት ጊዜ ባለው የብሄራዊ ባንክ የምንዛሬ ተመን ተሰልቶ ወደ ብር መለወጥ አለበት፡፡

• በውጭ ምንዛሬ ግብይት የደረሰ ኪሳራ ወይም የተገኘ ጥቅም የሚሰላበትን ዘዴና የውጭ አገር ገንዘብ ወደብር የሚቀየርበትን ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን ሁኔታ የሚወሰን መመሪያ ባለስልጣኑ ያወጣል፡፡

5.6.ከግብር ለመሸሽ የሚደረገውን ጥረት ስለመከላከል
ገቢን መከፋፈል
ስለማሸጋገሪያ ዋጋ
ከግብር ለመሸሽ የሚደረጉ ዕቅዶች
• በገበያ ዋጋ መርህ ያልተደረገ ማንኛውም ግብይት ሲኖር ባለስልጣኑ ትክክለኛውን የገበያ ዋጋ መሰረት በማድረግ ከግብይቱ ጋር በተያያዘ የሚገኘውን ትክክልኛ ገቢ ፣ጥቅም፣ ተቀናሽ ኪሳራ ወይም ማካካሻ ግብይቱን ባደረጉት ወገኖች መካከል ሊያከፋፍል ወይም ሊደለድል ይችላል፡፡ https://www.youtube.com/watch?v=fc8zAuMjtuc
ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

5.7.የንግድ ስራ ከተቋረጠ በኋላ በተገኘ ገቢ ላይ ግብር ስለሚከፈልበት ሁኔታ

 የንግድ ሥራ ከተቋረጠ በኋላ በሚገኝ ገቢ ላይ የሚወሰነው ግብር
ሀ) ታክስ ከፋዩ የንግድ ስራ ከተቋረጠ በኋላ የሚሸጣቸው እቃዎች የተሸጡበትን ዋጋ ማረጋገጥ የማይቻል ከሆነ እቃው የተገዛበት ዋጋ ወደ ሽያጭ ተቀይሮ ግብሩ ይወሰናል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

የንግድ ስራ ከተቋረጠ በኋላ…

 ለ) ታክስ ከፋዩ እቃውን የሸጠው የሒሳብ መዝገብ ለሚይዝ ታክስ ከፋይ ከሆነ እቃው የተሸጠበት ዋጋ ገዢው በሚያዘጋጀው የግዥ ማረጋገጫ ሰነድ (Purchase Voucher) መሰረት ይወሰናል፡፡
 ሐ/ የንግድ ስራ ካ ቋረጠ በኋላ የንግድ እቃ የሚሸጥ ታክስ ከፋይ የተርን ኦቨር ታክስ ሰብስቦ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

የንግድ ስራ ከተቋረጠ በኋላ…

 ታክስ ከፋዩ ድርጅቱን ሲዘጋ በእጁ ያሉትን እቃዎች ቆጥሮ ለታክስ

ባለስልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

 ሠ) ታክስ ከፋዩ ድርጅቱን ከዘጋ በኋላ በሸጣቸው እቃዎቹ የመዝገብ ዋጋ (Book Value) ከተሸጠበት ዋጋ ላይ ተቀንሶ በሚገኘው ልዩነት ላይ የሚሰላ ይሆናል፡፡

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

የሙከራ ጥያቄዎች

•1ኛ. በማዕድን ወይም በነዳጅ ስራዎች የተሰማራ ፍቃድ ያለው ድርጅት በተቀናሽ የሚፈቀዱለትን ወጪዎች ዘርዝሩ ?
•2ኛ. የንግድ ስራ ከተቋረጠ በኋላ በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር እንዴት ነው የሚወሰነው?

•3ኛ. ከግብር መሸሽ (tax avoidance) እና ግብር መሰወር (tax evasion) መካከል ያለውን ልዩነት አብራሩ ?

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ክለሳ(ማጠቃለያ)

• የቤት ኪራይ ገቢ ግብር
• የቤት ኪራይ ገቢ ግብር መጣኔ
• የንግድ ስራ ገቢ ግብር
• የንግድ ስራ ገቢ ግብር መጣኔ

• ተቀናሽ ወጪዎች
• የሂሳብ መዝገብ አያያዝ
• በግምት የሚወሰን ገቢ ግብር

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን

ማጣቀሻ (Referance)
•የገቢ ግብር አዋጅ ቁ . 979/2008
•የታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008
•የገቢ ግብር ደንብ ቁ . 410/2009
•የታክስ አስተዳደር ደንብ ቁ . 410/2009
•መመሪያ ቁ. 138/2010 ታክስ በግምት ስለሚወሰንበት ሁኔታ የወጣ መመሪያ
•መመሪያ ቁ. 152/2011 የሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ
•መመሪያ ቁ. 1/2011 ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች አፈፃጸም መመሪያ (የገንዘብ ሚኒስቴር) •መመሪያ ቁ. 5/2011 ስለ ተቀናሽ ወጪዎች የወጣ መመሪያ (የገንዘብ ሚኒስቴር)
•መመሪያ ቁ. 8/2011 የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ስለሚከፈል ግብር አፈፃፀም (ገንዘብ ሚኒስቴር)
•መመሪያ ቁጥር 146/2011146-2011 የንግድ ስራ ከተቋረጠ በኋላ በተገኘ ገቢ ላይ ግብር ስለሚከፈልበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ

ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚሆን